# በመዋዕለ ሕጻናት ውስጥ ወላጅ ስለመሆን



## በመዋዕለ ሕጻናት እና በልጆች ቤት መካከል ያለ የሥራ ትብብር

ሕጻናት ደስተኞች ሆነው እንዲያድጉ በልጆቹ ቤት እና በመዋዕለ ሕጻናቱ መካከል ቅርብ የሆነ የሥራ ትብብር መኖሩ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የመዋዕለ ሕፃናትን ይዘትና የሥራ ኃላፊነት መዋቅራዊ እቅድን በሚመለከተው የሕፃናት ሕግ እና ደንብ ውስጥ ከፍተኛ ክብደት ተሰጥቶታል። ጥሩ የሥራ ትብብርን ለማሳካት፣ በወላጆችና በመዋዕለ ሕፃናቱ መካከል የቅርብ ግንኙነት ሊኖር ይገባል። ግንኙነቱ የሚካሄደው በእየለቱ ሕፃንን በማድረስ እና በመመለስ ጊዜ፣ እንዲሁም  ስለ እድገታቸው በሚደረጉ ውይይቶች እና በወላጆች ስብሰባዎች ጊዜ ነው።

## አጀማመር

ከመዋዕለ ሕፃናቱ ጋር የሚደረገው የመጀመሪያ ግንኙነት ለወላጆችም ሆነ ለሠራተኞች አስፈላጊ ነው። መዋዕለ ሕፃናቱ ሕጻናት እና ወላጆች ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ደህንነት እንዲሰማቸዉና እና እምነት እንዲያድርባቸዉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ሕጻናት የተለያዩ ናቸው። መዋዕለ ሕፃናት ሲጀምሩ የሚያሳዩት ስሜትም የተለያየ ነው። አንዳንዶቹ ወዲያውኑ አዲሱን አካባቢ ሲላመዱ ሌሎቹ ደግሞ ለመላመድ ረጅም ጊዜ ይወስድባቸዋል።

መጀመሪያ ላይ ሕጻኑ ከአንድ ወይም ከሁለቱም ወላጆቹ ጋር በመሆን ለጥቂት ሰዓታት ብቻ ነው መዋዕለ ሕጻናቱ ውስጥ መቆየት ያለበት። ቀስ በቀስ ሰዓቱን መጨመር ይቻላል። የመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ዉሎ ምን መምሰል እንዳለባቸው መዋዕለ ሕፃናቱ ከእናንተ ጋር ይነጋገራል። በነዚህ ጊዜያቶች ለሕፃኑ በቦታው መገኘትና ተደራሽ መሆን አስፈላጊ ነው። ልትሄዱ ስትሉ ሁሌም አሳውቁ። እንዲሁም እናንተ ከሄዳችሁ በኋላ ለሕፃኑ እንክብካቤ የሚያደርጉት የመዋዕለ ሕፃናቱ ሠራተኞች መሆናቸውን ለሕፃኑ ንገሩት። ይህ ሕጻኑ ደህንነት እንዲሰማው፣ እንዲሁም በእናንተና በሠራተኞቹ ላይ እምነት እንዲኖረው አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ብዙዎቹ መዋዕለ ሕፃናት ሕጻናት መዋዕለ ሕጻናት እንደጀመሩ ከወላጆቻቸው ጋር ውይይት ማድረግ ይፈልጋሉ። ይህ ውይይት መዋዕለ ሕጻናቱ ከሕጻናቱጋር በደንብ እንዲተዋወቅ ይረዳል። ሕጻኑ በተለይ የሚያስፈልገው ነገር ካለም በዚሁ ውይይቱ ላይ መንገር ትችላላችሁ። ለምሳሌ ምግብን፣ እንቅልፍን እና የሚወዳቸውን ነገሮች በሚመለከት፣ ሕፃኑን ለመውሰድ የሚፈቀድለት ማን እንደሆነ፣ ወይም ሌሎች መዋዕለ ሕፃናቱ ትኩረት ሊያደርግባቸው ይገባል የምትሏቸውን ነገሮች። በውይይቱ ላይ መዋዕለ ሕፃናቱም ለእናንተ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመስጠት አጋጣሚ ያገኛል።












## የመዋዕለ ሕፃናቱን ይዘት የሚመለከት መረጃ

ሁሉም መዋዕለ ሕፃናት የመዋዕለ ሕፃናቱን የትምህርት አቅርቦቶች የሚገልፅ ዓመታዊ እቅድ አላቸው። በተጨማሪም መዋዕለ ሕፃናቶች በወርሃዊ ደብዳቤ ወይም ክፍሎች በሚልኩት ደብዳቤ መረጃዎችን ያሰራጫሉ። ሊደረጉ ስለታቀዱ ተግባራት፣ እንዲሁም የተከናወኑ ድርጊቶችን ስለሚመለከቱ ግምገማዎች በእነዚህ ደብዳቤዎች ላይ ያገኛሉ። ብዙዎቹ መዋዕለ ሕፃናት በየቀኑ የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች በፎቶግራፍ፣ በጽሁፍ፣ ወይም በሁለቱም መንገድ በማጠናቀር በየጊዜው በሰነድነት ያስቀምጣሉ። የተወሰኑ መዋዕለ ሕጻናት ደግሞ ለመረጃ ልውውጥ የሚገለገሉባቸው የዲጂታል ዘዴዎች አሏቸው።

## ኢመደበኛ ውይይቶች

በመዋዕለ ሕጻናት እና በወላጆች መካከል የሚኖሩት ብዙዎቹ  ግኑኝነቶች፣ ለምሳሌ ወላጆች ሕጻናትን ሲያደርሱና ሲወስዱ በልብስ መቀየሪያው ክፍል ውስጥ እያሉ የሚፈጠሩ ኢመደበኛ ውይይቶች  ናቸው። ይህ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ሌሎች ሕጻናትና አዋቂዎች በቦታው ይኖራሉ። እናም ሌሎች መስማት የሌለባቸውን ጉዳይ አንስተው መነጋገር ከፈለጉ፣ በግል እንዲያነጋግሯችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።



© Nina Honningsvåg Træet

## መደበኛ ውይይቶች

በዓመት ለሁለት ጊዜ የሕጻናቱን ዕድገት አስመልክቶ በሚደረገው አስገዳጅ ውይይት ላይ እንዲሳተፉ መዋዕለ ሕጻናቱ ይጋብዞታል። ይህ ውይይት በመዋዕለ ሕጻናቱ መምህራንና በእያንዳንዱ ሕጻን ወላጆች መካከል የሚደረግ ነው። በውይይቱ ላይ  የሕጻናቱን ፍላጎት፣ ደስተኝነት እና እድገት በተመለከተ እርስ በርስ መነጋገር ትችላላችሁ። ፍላጎታችሁ ከሆነ ለውይይቱ አስተርጓሚ እንዲያዝላችሁ መዋዕለ ሕፃናቱን  መጠየቅ ትችላላችሁ።

## የወላጆች ስብሰባ

በዓመት ከአንድ እስከ ሁለት ጊዜ መዋዕለ ሕጻናቱ ሁሉም ወላጆች የሚጋበዙበት የጋራ የወላጆች ስብሰባ ያደርጋል። በዚህ የወላጆች ስብሰባ ላይ መዋዕለ ሕጻናቱን የሚመለከቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ተነስተው ውይይት ይደረግባቸዋል። ሁሉም ወላጆች የራሳቸውን ሀሳብ ማቅረብ ይችላሉ።

## የወላጆች መማክርት ጉባኤ እና የትብብር ኮሚቴ

የወላጆች መማክርት ጉባኤ በመዋዕለ ሕጻናቱ የሚውሉ ሕፃናት ወላጆችን በሙሉ ያቀፈ ነው።  የወላጆች መማክርት ጉባኤ የወላጆችን የጋራ ፍላጎት ያራምዳል። እንዲሁም በመዋዕለ ሕፃናቱ እና በወላጆች ቡድኖች መካከል ያለው የሥራ ትብብር መልካም የመዋዕለ ሕፃናት አካባቢያዊ ሁኔታን እንዲፈጥር አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የትብብር ኮሚቴው (SU) ከወላጆች እና ከመዋዕለ ሕፃናቱ ሠራተኞች የተውጣጣ ነው። ኮሚቴው በመዋዕለ ሕፃናቱ እና በሕፃናቱ ቤት መካከል ጥሩ የሥራ ትብብር እንዲኖር ያደርጋል። ለመዋዕለ ሕፃናቱ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች፣ ለምሳሌ የዓመት የሥራ እቅድ፣ በጀት፣ የአሠራር ወይም የአደረጃጀት ለውጥ የሚታዩት በትብብር ኮሚቴው ነው።

Foto forside: © Asle Bentzen
Skipnes.no Svanemerket trykksak, 2041 0731

BERGEN
KOMMUNE